ተቃዋሚዎቸ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ አጭር
<u>የስራ እቅድ እና አቅጣጫ</u>

ጎዳር 11-2000 ዓ.ም

<u>መግቢያ</u>

የደርግ ሥርዓት ባደረግነው መራራ ትግል ተሸንፎ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ በአገራችን አዲስ የፖለቲካ - ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ችለዋል። ከዚህ የተነሳም አገራችን ለዘመናት በልማት - ዴሞክራሲና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ወደ ኋላ ስትሄድበት የነበረውን ሁኔታ ተቋርጦ፣ ልማትና ዴሞክራሲ የምታስመዘግብበት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በተለይ ከተሀድሶአችን በኋላ በኢኮኖሚው ዘርፍ ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ትገኛለች። የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት በዋናነት በእርሻ ላይ የሚታይ ቢሆንም በሌሎች ዘርፎችም እድገቱ የታየበት ሁኔታ ነው ያለው። የሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት በመአድን ላይ ተመሥርቶ የመጣ እድገት ሳይሆን መሠረታዊ ከሆነው የሀገራችን ሀብት፣ ጉልበትና መሬትን መሠረት ያደረገ ነው። ይህንን መሠረት በማድረግ ከገበያ ጋር ተቀናጅቶ የኢንዱስትሪ እድገት ሊያመጣ የሚችለው፣ በመሠረቱ የኢኮኖሚ መዋቅሩን በሚለውጥ መንገድ እየተካሄደ ስለሚገኝ እየታየ ያለው እድገት በዓለም ፈጣን ለውጥ እያስመዘገቡ ናቸው ከሚባሉት እኩል ተሰልፎ ፈጣን የሚባል እድገት እያመጣ በመሄድ ላይ ነው ያለው። ይህ ደግሞ በሌሎች ክልሎች እየተመዘገበ ያለ እድገት ብቻ ሳይሆን በትግራይም ከተሀድሶአችን በኋላ ከ10% - 14% በየዓመቱ የኢኮኖሚ እድገት እየመጣ ነው። የዚህ አብነት በየጣቢያው እየታየ ያለው ለውጥና በየከተማው እየታየ ያለውን የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ሥራዎችና የጉልበት ዋጋ መጨመር ዓበይት መረጃዎች ናቸው።

ይህ ደግሞ የሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት ፈጣን መሆኑ ብቻ ሳይሆን ህዝብ በየደረጃው የሚጠቀምበትም ነው። ገጠሩና እርሻ የእድገታችን ሞተር ሆኖ እያስመዘገበ ያለው እድገት - ዋናው ምንጩ፣ በከተማና ገጠር ያለው በእጁ የሚገኘው ጉልበት ስለሆነ፣ የጉልበቱ ባለቤት የሆነውምን ህዝቡ ስለሆነ የህዝቡ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ በመሆኑ በከተማ ይሁን ገጠር ያለው ህዝብ ተጠቃሚ መሆን የጀመረበት ሁኔታ ነው ያለው።

በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገው ትግልም በተተለመለት ስትራቴጅያዊ አቅጣጫ እየሄደ ከቀን ተቀን - ጥልቀትና ስፋት እያገኘ በመሄድ አለ። የህዝቦችና ዜጎች መብቶች ያለገደብ ሙሉ በሙሉ የሚረጋገጥበትና በሕግ የፀደቀበት ሁኔታ ስለአለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል አስፈላጊ የሆነው ቅድመ- ሁኔታ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስክ በሚያስተማምን ደረጃ እየተፈጠረ የሚሄድበት ሁኔታ አለ። በሀገራችን የተለያዩ አስተሳሰቦችና ጎብረተ-ሰብን የሚወክሉ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ተፈጥረው ነፃ ሆነው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ አለ። የመንግሥት አካላት በሕገ-መንግሥታችን መሠረት አንዱ ከሌላው ነፃ ሆኖ የተደራጀበትና በተግባርም የሥልጣን ወሰን (ገደብ) ተለይቶ የሥልጣን ወሰናቸውን አውቀው፣ ነፃ ሆነው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ባጭሩ ባገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት እየተሳካ የሚሄድበት አገባብ ተግባር ላይ እየዋለ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው። ይህም ከአዲሱ ሚለኔም ተዛምዶ በአዲስ ወኔና መንፈስ፣ በውስጣችን አንድነትና መቻቻልን ነግሶ የሚለኒየሙ የልማትና ዴሞክራሲ-ግቦች ለማሳካት ሁላችን ቃል የገባንለት በወኔ ተነሳስተን ፍጥነት ጨምረን ወደማያቋርጥ የእድገት ሂደት እንድንገባ መንግሥትና ድርጅታችን ቆርጠው የገቡበት ሁኔታ ነው ያለው።

ይህ ሆኖ ግን በልማት ይሁን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት ተተልመው ያሉትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ ተፈላጊው የህብረተ-ሰቡ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ዓበይት ሁለገብ እድገት የሚያመጡና ወደፊት መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ብቁ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች እንኳን ቢሆኑ ለዚህ ሊፈታተኑ የሚችሉ ችግሮች ግን ትናንሽ አይደሉም። አሁን እየታየ ያለው ለውጥ የሚያመለክተው ጉዳይ በሁለት ዓሰርት ዓመታት ሀገራችን ባልተራዘመ ጊዜ ውስጥ መሀከለኛ ገቢ (ምርት) ካላቸው ሀገሮች ጎን ልትሰለፍ የምትችልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር አስተማማኝ ቢሆንም ከፊታችን ተደቀነው እየተፈታተኑን ያሉት ችግሮች አንድ ባንድ ለይቶና ታግሎ ማሸነፍ ግን የግድ ነው።

የነፃ ገበያ ሥርዓት መገንባት አደጋ በተሀድሶአችን ወቅት በሚገባ ተብራርቶ መልስ የተሰጠበት ጉዳይ ነው። የዚህ ሥርዓት አደጋም የጥገኛ ኪራይ አካባች (ሰብሳቢ) አደጋም በዚሁ በኩልም ተያይዞ ሙስናና (ኮራፕሽንና) ፀረ-ዴሞክራሲ ዋና የሥርዓቱ አደጋ መሆኑ ተብራርቶ በየደረጃው ያለ አመራርና ህዝብ ከልብ የተረዳውና ያመነበት ጉዳይ ነው።

እዚህ ልንለው የፈለግነው የጥገኛ አስተሳሰብ የሚወክሉ የተደራጁና ያልተደራጁ ሥርዓቱን እንዴት መሸርሸር እንደሚችሉና አደገኛነታቸው፣ እንዲሁም የትግሉ አካሄድ ባለፉት ፅሑፎቻችንና ሥልጠናዎች በሚገባ ልናያቸው ችለናል። አሁን

ትኩረት ሰጥተን ማየት ያለብን ነገር ካለ፣ በክልላችን ተደራጅተው ሊንቀሳቀሱና ተጀምሮ ላለው የልማትና ዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ሊያደናቅፉ በኦፊሺያል ተደራጅቶ ያለው አንጃ ማንነትና በተሀድሶ ወቅት የነበራቸው አቋም፡ አሁን ተደራጅተው መንቀሳቀስ ለምን እንደፈለጉና የነዚህ መደራጀት ፋይዳው ለማየት ነው። በተጨማሪም እነዚህ በክልላችን ተቃዋሚ ፓርቲ ሆነው ሲሰሩ ካድሬአችንና አባላችንን አገባብ ባለውና በሌለው መንገድ እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለበት ለመጠቆም ነው። ድርጅታችን ህወሓት እነዚህ የሥርዓታችን ዴሞክራሲያዊነት የሚፈታተኑ አደጋዎች በተለይ በትምክህተኞች ጠባብ ኃይሎች የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሲያካሂዱት ለነበረው ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ህዝብ የሆኑ እንቅስቃሴዎች፣ ፀረ-ህዝብና ሕገ-መንግሥታችንን የሚፃረር አካሄድ ውሽትና ማጭበርበርን ለማስወገድ የቅርብና የሩቅ ትልሞች ተነድፈው ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ እንቅስቃሴ እየተደረገ ተጨባጭ የልማትና ዴሞክራሲ ለውጦች ለዚህ-የጥገኞችና ኪራይ አካባች አደጋ ለማምከን አመቺ-ሁኔታ እየተፈጠረ የሚሄድበት ሁኔታ ነው። ዞሮ ዞሮ የሥርዓታችን አደጋ በትምክሕት፣ ጠባብነት፣ ከባብያዊነት፣ .....ወዘተ. መልኮች እንደሚገለጸ ግልፅ አድርገናል።

በክልላችን ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለዓላዊነት (ክልላዊ ፓርቲ) ነኝ ብሎ ተደራጅቶ፣ የህወሓት ተቃዋሚ ፓርቲ ሆኜ እሰራለሁ የሚል የተደራጀ ቡድን **ኣለ**።

<u>ይህ ቡድን ማን ነው፡</u>

ይህ ቡድን በተሀድሶአችን ወቅት ድርጅታችን ራሱን ሊገመግም፣ ያለው ጠንካራ ጎን አይቶ በውስጡ የሚታዩ እጥረቶች ፈትሾ፣ በድርጅታችን ተሀድሶ እንደሚያስፈልግ ታምኖበት ይህንኑ ተግባር ላይ ለማዋል የህወሓት ማ/ኮሚቴ ተሰብስቦ የሥርዓታችን አደጋ ለይቶ ለማወቅና፣ በአንፃሩም አደጋው ራሱን ለማየትና ለመመርመር ቁጭ ባለበት ወቅት ስብሰባውን ረግጦ የወጣ አንጃ የተሰባሰበበት ድርጅት ነው። ይህ አንጃ ቡድንም የትምክህተና ጠባብነት ድርጅቶች እንደሚያደርጉት ከነሱ እኩል ወይም በከፋ መልኩ በድርጅታችን ላይ ጥላቻና ቅሬታ የፈጠረ፣ ለራሱ ሥልጣን አግበስብሶ - በያዘው ሥልጣን - በሀገራችን ቆራጭ-ፈላጭ የሆነ አምባገነናዊ ሥርዓት ለመመሥረት ተመኝቶ የነበረ ቡድን ነው። በፀረ-ዴሞክራሲ አቅጣጫ ህዝብንና ድርጅታችንን ለአደጋ ያጋለጠ ቡድን ነው። ድርጅት **ይበተን**፣ የትግራይ ህዝብ ጥቂትና ጫፍ ላይ የሚኖር ህዝብ፡ ለኛ ሥልጣን መያዝ መሠረት አይሆነንም ብለዋል። የሌላ አከባቢ የትምክህትና ጠባብነት አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ፣ ከዚህም አልፎ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣን ልይዙና ድርጅታችንን ሊያጠፉ ያልገለበጡት ድንጋይ አልነበረም። ሁሉንም ሞክረው መሆን ሲያቅታቸው፣ ይህ አንጃ አሁን የዴሞክራሲ፣ ለዓላዊነትና የትግራይ ህዝብ ጠበቃና ወኪል እንሆናለን ማለቱ ብዙ አያስገርምም። ለዚህ አንጃ አመቺ ሁኔታ የፈጠሩ አስተሳሰቦች ግልፅ ናቸው።

የትምክህት፣ ጠባብነት፣ ከባቢያዊነት፣ ቂምና ቅሬታን፣ ....ወዘተ. **ሁሉም በሥርዓቱ ላይ አደጋ ሊሆኑ የሚችሉ ኃላ-ቀርነትና ስሜቶች (የህዝቡም) ሊጠቀሙባቸው፣** ሞክሯል። በአከባቢያችንም፣ እነዚህ አስተሳሰቦችን በመጠቀም ጀምረነው ላለው የልማትና ዴመክራሲ ግንባታ ከህዝባችን ጋር ሁነን-ዓቅማችን ሁሉ-ልማትና

ዴሞክራሲን ለማስፋት የምናካሂደውን ትግል ለማደናቀፍ፣ ያለ-የሌለ ውሸትና አሉባልታ ተክነው እየተንቀሳቀሱ ናቸው። ሁላችን እንደምናውቀው በተሀድሶ ወቅት በድርጅታችን ህወሓት ያ የሥርዓታችን አደጋ የሆነው ጥገኝነትና የኪራይ አካባችነት አስተሳሰብ፤ ድርጅታችንን ለሁለት ከፍሎ በድርጅታችን ላይ ትልቅ አደጋ ያደረሰ አስተሳሰብ ይዞ፤ ከዚህ አልላቀቅ ብሎ ህወሓት እንድትበተንና እንድትጠፋ- ትልቅ በደል ያደረሰ አንጃ፣ አሁንም በተሀድሶ ወቅት ይዞት የነበረው አስተሳሰብ በመቀጠል ህወሓትን የመበተን ዓላማ ይዞ ከትምክህትና ሁሉም ፀረ-ህዝብ ኃይሎች ጋር በአስተሳሰብና በዓላማ አንድ ሆኖ፣ በውጭ- መገናኛ ብዙኃንና በውስጥ የግል ጋዜጦች እየተጠቀመ ተጀምሮ ላለው ፈጣን የልማትና ዴሞክራሲ የማስፋትና ጥልቀት የማግኘት እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ እየሠሩ ቆይቷል። አሁን ደግሞ በኦፊሼል ፓርቲ ፈጥሮ ትግራይ ውስጥ ሊሠራና ህወሓትንና የትግራይ ህዝብን ለማደናቀፍ እንቅስቃሴ ጀምሯል።

የትምክህትና ጠባብነት ኃይሎች ከውጭ ጥገኛ ኃይሎች ጋር በመሸረብ፣ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ተረግጧል፣ ዴሞክራሲ የለም፣ ኢትዮጵያ ባህር የላትም፣ ልማት የለም፣ ....ወዘተ. እያሉ፣ ገበያ ላይ ወጥተው እነዚህን በመሸጥ ዋጋ ሊያገኙና - ሀገራችን የውጭ እርዳታና ብድር እንዳታገኝ፣ ተቀባይነታችን እንዲያሽቆለቁል፣ ሀገራቸውን ክደው፣ መንግሥታችንን ለማጥላላት፣ ሀገራችን ውስጥ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዳያብብ፤ ጥገኞችና ወራሪዎች እንዲኖሩ የሚያስችል፣ የጥገኝነትና ኪራይ አካባችነትን ክፍተት በዴሞክራሲያዊ-ልማትና በአስተዳደር እንዳይደርቅ ከቅንጅትና ሌሎች ጠላቶች ጋር ሆነው ማደናቀፍ ሲያቅታቸው፣ ድርጅታችን ህወሓት ከኢህአዴግ ጋር በመሆን ይህንን በሳል የሆነ ስልት ነድፎ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ አገባብ ከተቋቋመ በኋላ፣ አሁን በመሀከል ወደ ሥልጣን መቆናጠጫ መንገድ ስላጡ፣ ዓረና ትግራይ ንዴሞክራሲን ለዓላማነትን ክልላዊ ፓርቲ ሆነው በኦፊሼል ተደራጅተው መንቀሳቀስ ጀምሯል። በመሠረቱ ዓላማቸው ለልማትና ዴሞክራሲ ሳይሆን በሆነ ይሁን መንገድ ሥልጣን ለራሳቸው ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ዓላማ አላቸው ብሎ ድርጅታችን አያምንም።

<u>ለምን ?</u>

1. **የስርዓታችን አደጋዎች ጥገኛ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ በኢዴሞክራሲያዊ አገባብ ለመበልፀግና ስልጣን ለመያዝ መሞከር ብሎም ከባለስልጣናት ጋር በመሞዳሞድ ለመበልፀግ መሞከር የመሳሰሉ የሙስና አደጋዎች ናቸው ተብሎ ሲታወቅ እና በዚህ መሠረት ግምገማ ይካሄድ ተብሎ ሲወሰን በማናለብኝነት ህዝቡን እና ድርጅታችንን በመናቅ ስብሰባ ረግጠው የወጡ ግለሰቦች ናቸው፡፡**
2. **ድርጅታችን ውስጥ ኢዴሞክራሲያዊነት እየተስፋፋ ነው ሰለዚህም ውስጣዊ ችግሮቹን ገምግሞ ለመፍታት መስራት አለበት ሲባል ድርጅታችን የጠራና ችግር የሌለበት ነው በማለት ስብሰባ በትነው የወጡ ግለሰቦች ናቸው፡፡**
3. **የትግራይ ህዝብ በተለይ ደግሞ የህወሓት ካድሬዎችና አባላቶች ተዉ፤ ህዝባችሁንና ድርጅታቹ እየከዳችሁት ነው ብለው ሲመክሯቸው እናንተ እኛን ልትመክሩን አትችሉም አጎብዳጆች(yes man) ናቹህ ብለው**

በማናናቅ፤ በተሰውት ጓዶች ብለው ሲማፀንዋቸው እንጃባቹ በማለት፡ ባህሪያቸውን በመሠረቱ እንደቀየሩ ያስመሰከሩ ሰዎች ናቸው፡፡

4. ሙስና የስርዓታችን አደጋ ሆነዋል፤ ውስጣችን እናጥራ ስንል ድርጅታችን ውስጥ ሙስና የለም በማለት ባይናቸው እያዩት ለመታገል ሳይፈልጉ ቀርተዋል፡፡
5. ስብሰባውን ረግጠው ከወጡ በኋላም ህዝባችንንና ድርጅታችን የጠባብና ትምክህተኛ ሃየሎች ሰለባ አድርገውታል፡፡ ገብሩ አስራት መስቀል አደባባይ ላይ አንጃው በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አንጃውን ወክሎ ለአመታት የታገለበትን የራስህን መብት እራስህ የመወሰን፤የህዝቦች የነፃነት መብት ወደጎን ትቶ “ኤርትራ ላይ የነበረን አቋም ስህተት ነበርና ይቅርታ አድርጉልን“ በማለት ግለሂስ ሲያደርግ የትምክህት ሃይሎች ግና ሁላችሁም እጅ ትነሳላቹ ብለው ለዓመታት ለህዝቦች ነፃነት፤ለሰላምና እኩልነት የታገለውን የትግራይ ህዝብንና ድርጅቱን ችግር እንዲደርስበትና እንዲዋረድ አድርገዋል፡፡የትግራይ ህዝብንና ድርጅቱን ለብቻው ተነጥሎ በጠባብና ትምክህተኛ ሃይሎች እንዲንቋሸሽ፤ እንደተገንጣይ አገርን እንደከዳና ለሉዓላዊነት እንዳልቆመ ኣድርጎ ለማሳየት ትልቅ ተራ የተጫወተ አንጃ ነው፡፡
6. የዚህ አንጃው አባላት ግትሮችና ምቀኞች ናቸው፡፡ የኢህአዴግን አመራር በዋናነትም ህወሓትን ከሌሎች ትምክህተኛ ሃይሎች ጋር በመተባበር ለማዳከምና ለማጥፋት እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሃይሎች ናቸው፡፡

ጸረ ትምክህትና ጠባብነት በሚደረጉት የዲሞክራሲና የልማት ትግሎች ላይ ትንፍስ ሳይሉ፤ ነገር ግን ድርጅታችንን ለማዋረድ ከማንም ጸረ መንግስትና ድርጅት ጋር ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ።

ባለፈው የ1997ዓ.ም ምርጫ ላይ ቅንጅትና አመራሮቹ የትግራይን ህዝብ ለይተው ይህ ህዝብ መጥፋት አለበት፤ በረሃ ይግባ በማለት፤ 'ትግሬ ወደ መቀሌ ንበረቱ ወደ ቀበሌ' እያሉ ሲያጨናንቁትና መቆምያ መቀመጫ ሲያሳጡት አንጃው ከነሱ ጋር በመቆም ለትምክህተኞች ግለሂስ ያደረገ እንጂ የቅንጅት ዘረኛ አካሄድ ለትግራይ ህዝብ የሚኖረው አደጋ አይተው ትንፍሽ ብለው ለመናገር ያልደፈሩ ሰዎች አሁን በምንም ዓይነት መለክያ የትግራይን ህዝብ የሚጠቅም ተግባር ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ይህ አንጃ ሁላችንም እንደምናውቀው የህወሓት ዓላማ ያገር ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳይ መሆኑ በመርህ ደረጃ አምኖና ተደራጅቶ ይታገል እንዳልነበረ በዚህ ሰዓት እነዚህ አገባቦችና መንገዶች ጠፍተውበት ምንያህል ወደኋላ እንደቀረ የሚያሳይ ነው፡፡

<u>አሁን ፍላጎታቸው ምንድ ነው</u>

ድርጅታችን ፈጣን ልማትና መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ እየተረባረበ ባለበት፤ ህዝባችን የልማት ተጠቃሚ በሆነበትና የልማቱን ውጤት ማጣጣም በጀመረበት፤ አባላችን ልማቱንና መልካም አስተዳደሩን ለማስፋት በየወረዳው በግልም ሆነ

በተደራጀ መልኩ እቅድ ይዞ ህብረተሰቡን አንቀሳቅሶ ትልቅ የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች ለመስራት በሚንቀሳቀስበት፤ ድርጅቱንም ለማጠናከር በሚሰራበት በዚህ ወቅት አንጃው መጥቶ ቁምነገር ለመስራትና የተጀመረው ፈጣን ልማት ለማገዝ ሳይሆን ህወሓት ለለአላዊነት የቆመ አይደለም፤ ለአገር ጉዳይ ግድየለውም፤ ከድሮም ጀምሮ ፀረ-ዴሞክራሲ ነበር እያለ ህዝቡን በማደናገር፤ በጠባብና ጎጠኛ አስተሳሰቦች የህዝቡን ስሜት በማንሳሳት፤ ትግራይ አላደገችም፡ የትግራይ ህዝብ ብቃት ያለው መሪ አላገኘህም፡ አየተጎዳህ ነው፡ ለዚህም እኛን ከመረጥክ ለፍላጎቶችህ እንቆማለን በማለት ስልጣን ላይ ለመውጣትና አንደገና ስልጣን ለመያዝ በመነሳሳት ላይ ይገኛሉ፡፡

ባሁኑ ወቅት ህወሓት ዓላማውን ለተተኪው ትውልድ በታቀደ አኳሃን ለማሸጋገር ከስር ጀምሮ ወጣት ጎበዝ ተማሪዎችን በመመልመል፤ በየደርጃው ስልጠና በመስጠት፤ አዲሱ ትውልድ በተግባር እየተፈተነ የስልጣን ሽግግሩን በፍጥነት ለማድረግ የሚያስችል ርብርቦሽ በሚያደርግበት ወቅት አንጃው የስልጣን ጥማቱን ለማርካት፤ ስልጣኑ ከ አዲሱ ትውልድ ለመቀማት ህወሓት እንዲህ ነበረ እንዲህ ነው፤ትግራይ ላይ ተቃዋሚ ያስፈልጋል፤ ለለአላዊነትህ ተነሳ፤ ቀይባህር የማግኘት መብት አለህ እያለ ያለፈበት የገሸዎች አስተሳሰብ ይዞ እንቅስቃሴ መጀመሩ የሚያስገርም ነው፡፡

አንጃው “መንግስት ለውጥ እያመጣ ነው፤ በዚህ መለኩ እኛም ልናግዝ እንችላለን፤ተሃድሶው ጥሩ ውጤት እያስገኘ ነው፤እኛ ተሳስተን ነበር፤መንግስታችንና ድርጅታችን ይቅረታ ሊያደርግልን ይገባል ” ብሎ ግለሂስ በማድረግ ስልጣኑ ወጣቱ ትውልድ እንዲረከበው የሚያደፋፍር ስራ መስራት በተሻለው ነበር፡፡ ነገርግን የአንጃው አባላት በተሃድሶውም ወቅት ቢሆን ራሳቸውን በመካብ የታጋይነት ባህሪያቸው ጠፍቶ የጥገኛ አስተሳሰብ ወርሷቸው የህግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ የትግል ሂደቱን ከመጨፍ ባለመቁጠር በአለባልታና በኋቀር መስፍናዊ አስተሳሰብ ተበክለው...
አፈፃፀምላይ የሚከሰቱትን ጉድለቶች ከሚገባው በላይ በማጋነን ህዝብ መብትህ ተጥሰዋል የዜጎች መብት እክል ገጠመው ወዘተ እያሉ የትግራይን ህዝብ በዘርና በጎጥ እንዲከፋፈል፤የትግራይ ህዝብ እርስበራሱ እንዲጠረጣጠርና ከድርጅቱ ጋር እንዲጋጭ ለማድረግ የሚሞክርዋቸው ነገሮች ናቸው፡፡ አንጃው በቂም በቀል ተነሳስቶ ስልጣን ለምን አላገኘሁም በማለት እሱ ያልተሳተፈበት እድገት የማይዋጥላቸው ከኛወድያ ሌላ ከየት ይገኛል አይነት አስተሳሰብ እንደሚያምኑ ህዝቡና አባሎቻችን አውቀው ህግና ፖለቲካዊ አስተሳሰብን መሰረት በማድረግ ሊታገልዋቸውና ዋጋ እንደሌላቸው ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

ይዘውት የተነሱት ሃሳብ በመሠረቱ ትምክህተኛ ሃይሎችና ሻቢያ ከሚሉት የማይለይ በመሆኑ የተሻለ አማራጭ እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ከነዚህ ሰዎች ምንም የተሻለ አማራጭ ይመጣል ተብሎ አይጠበቅም፤ ምንም ቁምነገርም የላቸውም፡፡ በጭፍን ህወሓት ላይ ያላቸውን ጥላቻና ቅሬታ ለመወጣት የትግራይን ህዝብ ደግሞ ድሮ መሪዎች ነበርን በሚል ሽፋን ሊያጭበረብሩትና ሊከፋፍሉት ብሎም ጀምሮት ያለውን ልማትና ዴሞክራሲ ሊያደናቅፉበት ብቻነው ሊሆን የሚችለው፡፡

ስለዚህ የአንጃው ፍሬ የለሽ ወሬ ልማታችን ላይና ዴሞክራሲችን ላይ ምንም አይነት ችግር እንዳይፈጥር አባላችን በውል ተረድቶ በጥበብና በዴሞክራሲያዊ አ'ኳሃን ህገን ተከትሎ አጥብቆ ሊታገል ይገባል፡፡

እነዚህ የልማታችንና የመንግስታችን አደጋዎች ናቸው፡፡የትግራይ ህዝብ አንድነቱን አጠንክሮ ድህነትን በማጥፋት፤ስራ አጥነትን በመቅረፍ፤ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በማስፈን አባላችን በሚገኝበት የስራገበታ ሁሉ ነቅቶ በመጠበቅ ህዝባችን እንዳይከፋፈል፤ የልማት ስራዎቻችን እንዳይተጓጎሉ፤ ህዝባችን ወሬና አሉባልታ ላይ እንዳይውል እነዚህን እየታገለ ልማቱን እንዲያፋጥንና መልካም አስተዳደርን እንዲያሰፍን አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ መታገል ያስፈልጋል፡፡

<u>እነዚህን የምንታገልባቸው አቅጣጫዎች ምንድናቸው፤</u>

1. በዋናነት ጀምረናቸው ያለንውን የልማትና መልካም አስተዳደርን የማስፈን አቅጣጫዎች በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ የከተማና የገጠሩ ህብረተሰብ ከዚህ ተጠቃሚ መሆኑ እንዲረዳ ማድርግ፤ ከዚህ መንግስት ውጪ ሌላ ከድህነት የመውጪያ በር እንደሌለው እንዲረዳና ህዝቡ ራሱ የስልጣን ባለቤት ሆኖ አንጃውንም ሆነ ሌሎች ሃይሎች የሚታገልበትን ትጥቅ እንዲይዝ ማድረግ ነው፡፡
2. ህዝባችን የስርዓታችን አደጋ ጥገኛ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ሳይለፉና ሳይጥሩ ከባለስልጣናት ጋር በመሞዳሞድ ባቋራጭ መበልፀግ መሆኑ በሚገባ እንዲረዳ ማድረግ፤አንጃውም የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ከሚያራምዱ ውስጥ ሆነው ነገርግን ዴሞክራሲ የለም እያሉ እየዋሹ መንግስታችንና ድርጅታችን ከውጭም ከውስጥም ተቀባይነት እንዲያጣና ህዝባችን እንዲደናገር እነሱም ተመልሰው ስልጣን እንዲይዙ የሚያደርጉት ጥረት መሆኑ ህዝባችን በትክክል እንዲረዳ ማድረግ፡፡
3. አባላችንና ካድሪያችን የተሰጠውን ተልእኮ ገጠርላይ የገጠር ልማት ፓኬጆችን በማስፈፀም ከተማላይ ደግሞ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ፓኬጆችን በማስፈፀም፤የቤቶች ግንባታና የአገልግሎት ዘርፉን ፈጣን በማድረግ፤መልካም አስተዳደርን በገጠርና በከተማ እንዲሰፍን በማድረግና ህዝቡ እያየው ያለውን ተስፋ እንዲሰፋ በማደረግ በድርጅታችን አላማ ላይ መተማመን(confidence) እንዲኖረውና ሌትተቀን ሰርቶ ሊለወጥ እንደሚችል አምኖ ወደስራ እንዲገባ አድርገን ለስራ በተነሳበት ወቅት ደንቃራ የሚሆኑት የአንጃው ጓላቀር አስተሳሰቦችን እንዲመክታቸው ማድረግ ነው፡፡
4. የእለትተለት ልማታዊ እንቅስቃሴዎችላይ፤ግምገማና ሂስ ላይና አጫጭር ስልጠናዎች ላይ የስርዓታችን አደጋ የሆኑትን ትግራይ ላይ በተለይ አንጃውና ጥገኛ ሃይሎች በስርዓቱ ተጎድተናል የሚሉት መሆናቸው ለይተን አውቀን ልንታገላቸው ይገባል፡፡
5. ዓላማዎቻችንና መርሆቻችንን መሠረት በማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ(formal and informal) ቦታ እንደሌላቸውና ከሻብያና ከጥገኛ ሃይሎች ባልተናነሰ መልኩ የትግራይ ህዝብ ጠላቶች መሆናቸውን ሁሉም ባገኘው አጋጣሚ ሊነግራቸው፤ ሊያቃልላቸውና ዋጋ እንደሌላቸው

ሊነግራቸው ይገባል። ታግለው እነሱ እስኪወጡ ድረስ የነበረበት ደረጃ ላይ ያደረሱት ስርዓት በቂም በቀል ተነሳስተው ወደኋላ ተመልሰው ሊያፈርሱት መንቀሳቀሳቸው ምንያህል መጥፎዎች እንደሆኑ ህዝባችን ተረድቶ ሊነግራቸውና አንክሮ ሊተፋቸው በሚያስችል አገባብ መሄድ።

<u>ዝርዝር ያፈፃፀም አቅጣጫዎች</u>

I. አንጃ ከሌሎች ጠባብ ትምክህተኛና ፀረ-ህዝብ ሃይሎች የማይለይ መሆኑ መላ አባላችን ተገንዝቦ የጋራ መግባባትላይ መድረስ።

1. እዚህ የተገለፁትም ሆነ በውጪ ሚድያ የሚያነሷቸው ጥያቄዎቻቸውና ሃሳቦቻቸው ምን እንደሆኑ ተረድቶ ድርጅታችን ከሚያራምዳቸው የልማትና መልካም አስተዳደር አጀንዳዎችና ሊደርስባቸው ካቀዳቸው ግቦች ጋር ሲነፃፀሩ ምንያህል ፀረ-ህዝብና ፀረ-ልማት መሆናቸው አይቶ ያላቸውን ጉድለት ጠንቅቆ እንዲያውቀው ማድረግ።
2. የአንጃውን ኋላቀርነት አውቆና ተረድቶ ደጋፊና አባላቶች ሊያደርጋቸው እየመለመላቸው ያሉትንም ሰዎች ኮንኖ ከድርጅቱ ጎን በመቆም ልማትና መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ድርጅቱን በማጠናከር ዙርያ ላይ ተደራጅቶ መታገል ይኖርበታል።
3. አባላችን በግልና በመንግስታዊ ድርጅቶችና የመኖሪያ አከባቢዎች ተደራጅቶ የሚገኝ እንደመሆኑ የአንጃውን ማንነት በመሠረታዊ አደረጃጀቱ በኩል ተወያይቶ ከተረዳ በኋላ በሚሰራበትና በሚኖርበት አከባቢዎች ሁሉ የነሱን መጥፎነት ለማስረዳት፤ኑሮውን ለመኖር አቅዶ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ፤ እነዚህም የልማቱና የሰላሙ ደንቃራዎች መሆናቸውን አውቆ በሚኖርበትና በሚሰራበት አከባቢ ሁሉ ሰዎችን በማስረዳት፤ የነሱን ድክመቶች በማሳየት የማይጠቅሙትና ጭራሽ እንቅፋት መሆናቸው ማሳወቅ።

II. አንጃም ይሁን ሌሎች ፀረ-ሠላምና ዴሞክራሲ ሃይሎች ለሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የዕለትተዕለት ክትትል እንዲያደርግ ማድረግ።

1. አንጃ ምን እየተናገሩ ነው፤ የት ተናገሩ፤ ማንን ተናገሩ፤ ማንን እያገኙ ነው የሚለውን ሁሉ በሚኖርበት አከባቢና በሚሰራበት አከባቢ በጥብቅ ተከታትሎ ደጋፊ ለአባል፤ አባል ለቡድኑ፤ የቡድን መሪው ለመሠረታዊ አደረጃጀት መሪ ፤የመሠረታዊ አደረጃጀት መሪ ለወረዳ፤ ወረዳ ለዞንና ለክልል በፍጥነትና በየጊዜው ሪፖርት ያድርግ።

2. የአንጃ አባላትና ደጋፊዎች እነማ፤ ምን እየሰሩ፤ የት እየሰሩ፤ እንዴት እንደተደራጁና እንደሚገናኙ በስልክ በጽሁፍ በአካል የየአካባቢው ጥናት ሰንሰለቱን ጠብቆ በፈጥነት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

III. አንጃውንና አስተሳሰባቸውን በሚገባ መታገልና ማጋለጥ አለበት

1. አንጃው በሚጠራቸው ስብሰባዎች አባላችንና ደጋፊያችን በመገኘት ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ ገብቶ የሚሉትን በንቃት ተከታትሎ ሊታገላቸውና ሊያከሽፍባቸው ይገባል።

2. በእቅድ ደረጃ ሊመለምልና ደጋፊ ለማድረግ በአባልነት ተይዞ ያለው ሰው እነዚህን ሊያውቃቸውና ሊያስረዳቸው፤ ፀረ-ልማትና ዴሞክራሲ መሆናቸውና ከቅንጅት ሻቢያና ሌሎች ጠላቶች የማይለይ አስተሳሰብ እንዳላቸው፤ህወሓትን በቂምና ቅሬታ ተነሳስተው እያካሄደ ካለው ልማት ለማደናቀፍ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ማስረዳትና እንዲታገሉት ማድረግ፡፡
3. አባላችን ጎረቤቱ፤ ቤተሰቡና ሌሎችም በነዚህ እንዳይደናገሩ የትግራይም ህዝብ ልማቱ እንዳይደናቀፍ ጠላቶቹን ሊመክት፤ልማትና መልካም አስተዳደር ላይ ፈጣን ለውጥ ሊያመጣና ኑሮውን ሊያሻሽል እንደሚገባ ሰፊ ማነሳሳት ማደረግ፡፡
4. በዚህ መልኩ የአባልና ደጋፊው ቤተሰብና ጎረቤት ካመኑበት በኋላ ይሄን ተልእኮ ይዘው ማህበራት ላይና የልማት ቡድኖች ላይ ገብተው አባሉና ደጋፊው የጀርባ አጥንት ሆኖ እየመራ ማህበራቶቹንና የልማት ቡድኖቹን ሲያንቀሳቅስ እነዚህን ማህበራትና የልማት ቡድኖች በመጠቀም ህዝቡ የነዚህን ፋይዳና ዓላማ ተረድቶ ጠንክሮ እንዲታገላቸውና የልማት መደቦችን እንዲያፋጥን ማድረግ ነው፡፡
5. ትምህርትቤት ላይ፤ የመንግስት መስሪያቤቶች ላይና ሌሎች ድርጅቶችም ላይ በተመሳሳይ መልኩ አባሎቻችን ሁለትም ቢሆኑ ሶስት ተደራጅተው ከደጋፊዎቻቸው ጋር በመሆን ትምህርትቤት ላይ የህወሓትን ታሪክ ያልተረዳውን ለጋ ወጣት እንዳያደናግሩት ትኩርት ሰጥቶ ማስረዳትና የማይረቡ መሆናቸው፤የትግራይን ህዝብ ከፋፍለው የቅንጅትና ሻቢያ ሰለባ ሊያደርጉት እንጂ ሌላ ምንም ሃሳብ እንደሌላቸው፤ እንዳውም መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍንና ወደ አዲሱ ትውልድ ስልጣን ለማሸጋገር የተያዘውን አላማ ወጣቱን በማደናገር ስልጣን እንዳይረከብ የሚያደርግ ተግባር መሆኑ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

IV የአንጃዉና የሌሎች ጸረ-ልማት ሀይሎች አስተሳሰብና እንቅስቃሴ በተለያየ መልኩ መታገል

1. የነዚህ ባህሪ አያይዞ ምን እንደሆነና በተሃድሶ ወቅት የነበራቸዉ አስተሳሰብ ወይን ጋዜጣ ላይ በየጊዜዉ እየተጻፈ ወደመሰረታዊ ድርጅቶች አባላት እንዲሁም ወደህዝብ እንዲቀርብ ማድረግ

2. በዜና ማሰራጫ ሰፊ መግለጫዎች በከፍተኛ የአመራር አባላት ከታሃድሶ በዉህላ የታዩ ለዉጦች፣ መስመራችንና አላማችን ምን እንደሆኑ እንዲሁም የዚህን ስርአት አደጋ ህዝብና አባል እንዲያዉቀዉና እንዴት መታገል እንደሚገባ ማብራርያና ቃለመጠይቆች እንዲደረግ ማድረግ

3. ካድሬና አባላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ (formal and informal) አገባብ በመጠቀም በወጉ እንዲታገሉ ማድረግ፡፡ ይህም ማለት ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አላማ የሌላቸዉና በቂም በቀልና ቅሬታ ተነሳስተዉ ወደ ትልቅ ዉድቀት ገብተዉ ይሄን ድርጅት ለማፍረስ

የሚንቀሳቀሱ መሆናቸዉና ከቅንጅት፣ ከሻእብያ እንዲሁም ሌሎች መንግስታችንን ለማዳከም ከሚጥሩ ጋር በማነጻጸር የሚሉት ነገር ከዚህ የተለየ ቅንጣት ነገር እንደሌላቸዉ የማስረዳትና የማሳመን ስራዎች መስራት፡፡

በተጨማሪም አድሀሪ ሀይሎች ቀን ተቀን በሚታዩ ድክመቶቻችንና ኋላ ቀር በሆነ የህዝብ ስሜት ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም፣ ለምሳሌ ትግራይ አልለማችም፣ እንደርታ ተጎዳች፡ ሁሞራ ሰዉ አጣች ወዘተ፡፡ ይህንን በቀን ተቀን የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም ከአሁን በፊት በህወሓት ጽ/ቤት የተሰራጩ ጽህፎችና ወይን ጋዜጣ ላይ አዲሱ ራኢና የህዝብ በልማት ዉጤት ተጠቃሚነትን የሚገልጹ ጽህፎችን በማጣቀስ የትግራይና የህወሓት ተቀባይነት በሌሎች ድርጅቶችና ክልሎች ዘንድ እንዳይቀንስ ለአባሎቻችን እንድናስረዳና ህዝባችን እንዳይደናገር ማሳመን መቻል አለብን፡፡

ሌላዉ ከተለመደዉ አሰራር ዉጪ (informal) በምናደርገዉ እለታዊ እንቅስቃሴዎች አንጃ የሚያናፍሰዉ ወሬ ምን ያህል ጸረ-ዲሞክራሲና ምግባረ-ብልሹ መሆናቸዉና ለምሳሌ የስየ ጉዳይ በተገኘዉ መረጃዎችና ዘርፎ ባከማቸዉ ሀብት ፍርድ ቤት የ 6 አመት እስራት እንደተፈረደበት ሆኖም ግን ምንም ወንጀል የለብኝም ብሎ የሚያስወራዉ ሀሰት መሆኑ እያስረዱ መሄድ፡፡

አንጃ የሚመርጣቸዉና ቀርቦ የሚያነጋግራቸዉ ሰዎች ማንነት ማወቅ፡፡ ለምሳሌ በተለያየ ምክንያት የተባረሩና የተቀጡ ሰዎች እያፈላለገ እንደሚገናኝ በሌብነት ወይንም በሀሰት ተጠምደዉ ህዝብን የማይጠቅሙ በመሆናቸዉ ከአባልነትና ከትግል የተባረሩ ወይንም ድክመት ያሳዮትን እያፈላለጉ የመመልመልና የማደራጀት ስራ እያከናወኑ መሆናቸዉ ማሳየት፡፡

ገብሩ አስራት መስቀል አደባባይ ላይ ያደረገዉ ግለ ሒስ በመታገሉ እንደተጸጸተና አሁን ደግሞ ለዉጭና ለግል ጋዜጦች ለዚያ ላደረግነዉ ፍትሀዊና ዲሞክራሲ ትግል፣ ለከፈልነዉ መስዋእትነት የህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን፡ እኩልነትን ትቶ ልክ እንደ ቅንጅትና ሌሎች ሀይሎች፡ በግል የመወሰን መብት ተቃውሞ የነበረንን እምነት ሊያበላሽ ይሄንን መርጦ እዚህ ያደረሳትን ድርጅት ሊያፈርስና ለትግራይ ህዝብ ልክ እንደ ሻእብያ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ለማጣላት በር የሌላት፣ ባህር የሌላት ኢትዮጵያ የሆነችዉ በህወሓት ምክንያት ነዉ በማለት እየተናገረና እየጻፈ ነዉ፡፡ ይህንን አግባብ ባለውና አግባብ በሌለው መንገድ ህዝብ እንዲያዉቅና ባጠቃላይ ደግሞ አንጃ ጸረ-ህወሓትና የትግራይ ህዝብ መሆኑ ከተህድሶ ጀምሮ እስካአሁን የሚያረገዉ እንቅስቃሴ ተረድቶ ለነዚህ ጸረ-ህዝብ እንደአማራጭ ድርጅት ሆነዉ በትግራይ እንዲቀሳቀሱና ሊደራጁ ሞራል እንደሌላቸዉና እንደማይደግፉቸዉ ለማድረግ መቻል አለብን፡፡

V. በዚህ ስርአት ተጠቃሚ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል በጥቃቅን ችግሮች ወይ በማታልል ቂምና ቅሬታ ያለዉ የቀድሞ ታጋዮችን የነዚህ መጠቀምያ ከመሆን ነፃ ማውጣት፡፡

1. የነዚህ መጠቀምያ ሊሆን የሚችል በየጣብያዉ ማን ለምን መሆኑ ማጥናት በየወረዳዉ እንዲደራጅ ማድረግ፡፡
2. ቅሬታ የተሰማቸውን የቀድሞ ታጋይ አባላት ካጠናን በኋላ ምን መስራት እንደሚችሉ ከነሱ ጋር በመግባባት ተደራጅቶ በግላቸዉ ምን እንደሚችሉ በመግባባት የስራ እድል የሚያገኙበትና አምርተዉ ራሳቸዉን የሚጠቅሙበት ሁኔታዎች መፍጠር፡፡
3. አባሎቻችንና ታጋዮቻችን እስካሁን ያካበትቸዉና አሁንም ያሉትን ጥሩ ልምዶች እንዲስፋፉና ልማት ላይ እንዲዉሉ አድርጎ የማንም ፀረ-ህዝብ ሃይል መጠቀምያ እንዳይሆኑ ቅስቀሳ በማድረግ እንዳውም መስዋዕት ከፍለውና የአካልጉዳት ደርሶባቸው ለታገለሉት ትግልና ዓላማ በህይወት እስካሉ ድረስ ሊታገሉለት እንደሚገባ በግልም ሆነ በየጣብያው መግባባት ላይ እንዲደረስ ማድረግ፡፡

N.B ይህ ፅሁፍ አጭር የመነሻ ሃሳብና እቅድ እንዲሆን ለወረዳና ዞን እየላክንላቹህ ነው፡፡ከአከባብያቹህ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም እቅድ አውጥታቹህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ እንድትገቡና በበለጠ ደግሞ በስልክና በደብዳቤ እየተገናኘን ስራዎቻችንን ልናፋጥን ይገባል፡፡

የህወሓት ጽ.ቤት
መቐለ

በህወሓት መመርያ ላይ

የትግራይ ዲሞክራሲዊ ትብባር
መግለጫ

በአሁኑ ወቅት የኢህአዲግ አምባገነን አገዛዝ በሚያራምደዉ ኢዲሞክራሲዊ የከፋፍለህ ግዛ ስርአት እንዲሁም በሚከተለዉ ኣድርባይና ጥገኛ የሆነ ፖሊሲ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ በድህነት አዘቅትና ኣስከፊ ጭቆና ስር እየማቀቀ እንዲኖር ተገደዋል። ከዚህ አልፎም የአገሪቱን አንድነትና ሉአላዊነት በከፍተኛ ፈተና ዉስጥ የሚገኝበት ወቅት መሆኑ መላዉ ህዝባችን የሚያዉቀዉ አሌ የማይባል ሀቅ ነዉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ህዝባችን ይህን አገዛዝ በመቃወም መጠነ=ሰፊ ተቃዉሞ በማድረግ የኢህአዲግ አገዛዝ አንቅሮ የተፋበትና ኢትዮጵያና ህዝቦችዋ በዘር የሚከፋፍል ፀረ ዲሞክራሲ ፀረ አንድነት ፀረ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሆነ አምባገነን ስርአት መቸም ቢሆን እንደማይቀበል በተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎችና ስብሰባዎች ተቃዉሞ ሲገልፅ ኣያሌ ሰቆቃ ኣሳልፈዋል። በተለይ ደግሞ ከጉንቦት ምርጫ ወቅት

ጀምሮ ኣለም=ኣቀፍ ታዛቢ በተገኘበት በአደባባይ ተቃዉሞዉን ያስመሰከረበት ከመሆኑም አልፎ ለወደፊትም ቢሆን ጎሳን መሰረት ያደረገ ኣገዛዝ፤ የህዝቦችዋን ለኣላዊ ጥቅም የማይጠብቅና ለጠላቶችዋ በር የሚከፍት ስርአት እንደማይፈልግ በከፍተኛ ተጋድሎ እየገለፀ ያለበት ወቅት እንገኛለን። የኢትዮጵያ ህዝብ ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ ኣፈር አማራ ትግሬ ኦሮሞ ጉራጊ ወላይታ ወዘተ ሳይል በደጉምበክፉም ለዘመናት አብሮ በአንድነት አገሩን ጠብቆ የኖረ ህዝብ፤ ለወደፊትም የሚኖር ህዝብ ነዉ። ይሁን እንጂ ኢህአዲግና የመለስ አምባገነን መንግስት እያራመደ ያለዉ ኢዲሞክራሲዊ ስርዐት የስልጣን ዘመኑ ሊያራዝምለት የሚችልዉ የጎሳ ፖለቲካ መሰረት ባደረገ አገዛዝ የህዝቡን አንድነት እየተፈታተነው ይገኛል። ይህ እኩይ አላማ ለመተግበር ደግሞ ማንኛዉም እርምጃ ከመዉሰድ እንደማይቦዝን በተደጋጋሚ ያየነዉ ጉዳይ ነዉ። ለዚሁ ይጠቅሙኛል ከሚላቸዉ የዉስጥም ይሁን የዉጭ ጠላቶችዋ አብሮ ተባበሮ እየሰራ ይገኛል። ይህ ስግብግባዊ ኣሰራር ለኣድርባዮችና ለጽንፈኞችም ኣመቺ ሁኔታ ፈጥረዋል።

ይሁን እንጂ ይህ እኩይ አላማ ዛሬም ይሁን ነገ አርቆ አሳቢ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንካራ የተባበረ ክንድ እንደሚሰባበርና ጠላቶችም እንደሸክላ ተንኮታኩተዉ እንደሚወድቁ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር ድርጅት ያምናል። ለዚህ ጥልቅ እምነቱም ይታገላል።

የመለስ አምባገነን መንግስት ኢትዮጵያን ያላበሳትን ውስብስብ ችግር አልበቃ ብሎት ለሚከተለዉ አፋኝ ስርአት ተቀጥያ የኣፈና መሳርያ አካል የሆነ መመርያ በቅርቡ አዉጥቶ በትግራይ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። መቐዉንም ትግራይ የኣፈናው ሙከራ=ጣብያ ሆነዋልና። መመርያው በትግርኛ **<u>ተቃዋምቲ ንዝገብርዎ ምንቅስቃስ ሓፂር ናይ ስራህ ትልምን ኣንፈትን</u>**፡ በአማርኛ ሲተረጎም **<u>ተቃዋሚዎች ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ አጭር የስራ እቅድ ና አቅጣጫ</u>** ይላል። ይህ መመርያ በድብቅ ሲሰራበት የቆየ አዲስ ባይሆንም እንደአዲስ ተፅፎ "ህጋዊ" በሆነ መንገድ የወጣዉ አሁን ሲሆን መመርያዉ የሚያትተዉ የኢህአዲግ ካድሪዎቹና ተከታዮቹ እንዴት ተቃዋሚዎችን ማፈን፤ ማሰር፤ ማሰቃየት፤ ወዘተ እንዳለባቸዉ የሚዘረዝር ፅሁፍ ነዉ። የመለስ ቡድን ይህን የኣፈና መመርያ በቅርቡ ኣሰራጭቶ ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ይህ ባለ14 ገፅ መመርያ የኣፈና ኢላማ ያደረገዉ በቅርቡ በምርጫ ቦርድ እዉቅና አግኝቶ በትግራይ ክልል በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ **አረና ትግራይ ለፍትህ ለዲሞክራሲ እና ለአንድነት** የተባለ ፓርቲ ወይም ድርጅት ሲሆን ኣጠቃላይ አላማዉ ግን በማንኛዎም የኢትዮጵያ ክልል የሚንቀሳቀሱ ማንኛዉም የተቃዋሚ ፓርቲዎች በተመሳሳይ መንገድ ለማፈን መሆኑ የትግራይ ዲሞክራሲዊ ትብብር (ትዴት) አበክሮ የተገነዘበው ጉዳይ ነው። በመሆኑም ትዴት ይህን አይነት አፋኝ ፀረ=ዲሞክራሲ የግፈኞች አሰራር አጥብቆ የሚያወግዘዉና የሚቃወመዉ መሆኑ ይገልፃል።

በመመርያው ፅሁፉ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ፡

1. ኣረና ትግራይ ጸረ=ልማት፡ ጸረ=ዲሞክራሲ፤ ለትግራይን ሕዝብ አደገኛ ጠላት ነው በማለት ልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ አንዱ መንግስታዊ ግዴታ መሆኑ ቀርቶ

እንደማስፈራርያና ህዝቡን ያለበት ኢኮኖሚያዊ ችግር እንደመያጣ ይጠቀምበታል። ያሰጠነቅቃልም።

2. ፓርቲዉ ህጋዊ ድርጅት ቢሆንም የመለስ (ኢህአዲግ) ስርአት ግን ማንኛዉም በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ መልክ የሚንቀሳቀስ የተቃዋሚ ድርጅት አመራርና ደጋፊ እንዴት ለስርአቱ አደገኛ እንደሆነና ሲንቀሳቀሱ እንዴት ህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ማፈን ማንገላታት እንዳለባቸዉ ይገልፃል

3. ከሌሎች የኢትዮጵያ ተቀዋሚ ድርጅቶች አብሮ በመሰለፉና በመቀራረቡ እንደ ክፋት ተቆጥሮ የትግራይ ህዝብን በጎሳነት ምክንያት ለማጥፋት የተንቀሳቀሱትን ይደግፋል በማለት መሰሪ መልእክት ያስተላልፋል።

4. ኢህአዲግ (ህወሓት) ለአገር አንድነትና ሉአላዊነት አልቆመም በማለታቸዉ የትግራይ ህዝቡን ጥቅም አደጋ የሚከቱ እንደሆኑ ኣስመስሎ ያቀርባቸዋል።

5. የትግራይ ህዝብ በድህነት እንደሚገኝና ምንም የልማት ጥቅም እንዳላገኘ የሚያወሩ ጠላቶች ናቸው ብሎ ይከሳቸዋል።

6. በመሆኑ ማንም የፓርቲዉ አባል ከማን ጋር እንደሚገናኝና እንደሚያወራ፣ እነማን የፓርቲዉ ተከታዮች እንደሆኑ፣ ማንን እንደሚመለምሉ በመከታተል መዋቅሩን አውቆ ተከታሎ ሁሉ ካድሪና ደጋፊ ሪፖርት እንዲያደርግ፣ በዚያውም አግባብ ባለውና አግባብ በሌለው መንገድ እንዲታገላቸው መመርያ ይስጣል።

7. በመጨረሻ መለስ ዜናዊ ከሚመራዉ ህወሓት (ኢህአዲግ) ፓርቲ ዉጪ ሌላ ፓርቲ በትግራይ እንደማያስፈልግ ይደመድምና በተመሳሳይ መልኩም በመላ ኢትዮጵያ ይህነኑ ሁኔታ እንዲፈጠር ያልማል።

ይህ በግልፅ የሚያሳየዉ የመለስ ኢህአዲግ ስርአት ስለ ዲሞክራሲ በተደጋጋሚ የሚያወራዉና የሚለፍፈዉ ለይስሙላ መሆኑ ጋህድ ያደረግ ሀቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዲሞክራሲና ለኣማራጭ መፍትሄ የቆሙትን ሁሉ ጠላቶች ተቆጥረው የኣፈና ኢላማ መሆናቸው ነው። ለመሆኑ የትግራይ ህዝብ እንደሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ኢትዮጵያዉያን የመሰለዉና ይጠቅመኛል ብሎ ያመነበት ሰዉ ወይም ፓርቲ አባል በመሆን የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመምረጥ መብቱን ለመጠቀም ለምን ይከለከላል? ወይስ የትግራይ ሕዝብ የመለስ ቡድን ኣምባገነናዊ ፖሊሲ በስተቀር ዴሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቱ መጠቀም ስለማያስፈልገዉ ነዉ? እዉን የአረና=ትግራይ=ለዲሞክራሲ=ለፍትህና=ለሉአላዊነት አመራር እና አባሎች የትግራይ ህዝብ ጠላቶች፣ የህዝቡን ጥቅምና አንድነት ለማፍረስ የተነሱ ናቸዉን? ትክክለኛ መልሱ የትግራይ ህዝብ ይስተዋል ብለን አናምንም። ለ17 ኣመታት መላ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱ ተገፎ በድህነት ውስጥ ተዘፍቆ ያኖረው የመለስ ስርኣት ነው። ይህም የትግራይ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠብቆለት በሰላም በአንድነት ለዘመናት የታገለለትን ዴሞክ/ዊ ስርኣትና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ከመታገል ወደ ሃላ እንዳላለና እንደማይል ጠንቅቀን እናዉቃለን።

በርግጥ ከኣምባገነኑ ኢህኣዴግ (የመለስ) መንግሰት ባ፫ገር ለግል ጥቅም ብቻ የቆሙ ኣድርባዮችና ኣርቆ ማየት የተሳናቸው ጽንፈኞች የህዝቡ የሚየደርገዉ ትግል በመበረዝ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ራሱ መርጦ የሚየስቀምጠው ስርኣተ=መንግስት እንዳይገነባ ደንቃራ እንቅፋት ሆነውብታል። ይሁንእንጂ ከመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ኣብሮ ነገሮቹን መርምሮ ኣሰፈላጊ በሆነ ኣቅጣጫ እየታገለ እንደሚጥላቸው ኣንጠራጠርም።

በተመሳሳይ በኣገር ቤትና በዉጭ የሚንቀሳቀሱ ተቀዋሚ ድርጅቶችም የወቅቱ ትግል ኣቅጣጫው ትብብርን የሚጠይቅ ከባድ ስራ በመሆኑ የህብረት/የጥምረት ወይም የውህደት ቅንብር በመፍጠር ኣይቀሬው የኣምባገነኖቹ ውድቀት ማቀላጠፍ ይኖርባቸዋል እንላለን።

ውድቀት ለኣምባገነኖች!
ድል ለዲሞክራቶች!!!

የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር
ለካቲት 2008